አስተያየት

FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

Draft

FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

Education and Training Authority

መመሪያ ቁጥር……………

## የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የጥራት ኦዲት መመሪያ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የጥራት ኦዲት መመሪያ ቁጥር -------/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011፣ የሚንስትሮች ምክር ቤት የባለስልጣኑን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን ባወጣው ደንብ ቁጥር 515/2014 እና የቴክኒክና ሙያ አዋጅ ቁጥር 954/2008 ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንዳሉ ሆነው በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1/ “ደንብ” ማለት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 515/2014 ነው፤

2/ “ተቋም” ማለት የመንግስት እና የግል የከፍተኛ ትምህርት ወይም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ተቋም ነው፤

3/ "የከፍተኛ ትምህርት" ማለት በቅድመ እና ድህረ ምረቃ ደረጃ የሚሰጥ ትምህርት ነው፤

4/ "ጥራት ኦዲት" ማለት ተቋማት የዘረጉት የውስጥ ጥራት ማረጋገጫ ስርዓት እየተተገበረ እና ውጤታማ መሆኑን የሚረጋገጥበት ግምገማ ነው፤

5/ "የውስጥ ጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት" ማለት ተቋማት የሚሰጧቸውን የትምህርት ወይም ስልጠና ጥራት ለማስጠበቅ የሚዘረጉት እና በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ የውስጥ ጥራት ማስጠበቅ ስርዓት ነው፤

6/ "ግለ-ግምገማ" ማለት ተቋማት በጥራት ማስጠበቂያ የትኩረት መስኮች መሠረት ራሳቸውን በመገምገም ያላቸውን ጥንካሬና ክፍተቶች የሚለዩበት ግምገማ ነው፤

7/ "የግለ-ግምገማ ሪፖርት" ማለት የተቋማትን አጠቃላይ የግለ ግምገማ ሂደት፣ ውጤትና በግለ ግምገማው የተገኙትን ክፍተቶች የሚያስተካክሉበት ቀጣይ እቅድ የያዘ ሪፖርት ነው፤

8/ "የጥራት ኦዲት ገለፃ" ማለት የጥራት ኦዲት ከመከናወኑ በፊት ለተቋሙ ስለ ጥራት ኦዲቱ ዓላማ እና ውጤት፣ ሂደት እንዲሁም ለጥራት ኦዲት ስለሚደረግ አጠቃላይ ዝግጅት የሚደረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ ነው፤

9/ "የጥራት ማጎልበቻ እቅድ" ማለት ተቋማት በግለ ግምገማ ሂደት የለዩዋቸውን እና በጥራት ኦዲት ተለይተው ምክረ ሀሳብ የተሰጠባቸውን ክፍተቶች ለማሻሻል የሚያዘጋጁት እቅድ ነው፤

10/ "የጥራት ኦዲት ክትትል ግምገማ" ማለት የጥራት ኦዲቱ ምክረ ሀሳቦች በሚጠበቀው ደረጃ ስለ መተግበራቸው ለማረጋገጥ የሚደረግ ግምገማ ነው፤

11/ "የውጭ ጥራት ኦዲተሮች" የባለስልጣኑ ቋሚ ሰራተኞች ያልሆኑና የኦዲተርነት ስልጠና ወስደው በጥራት ኦዲት ስራ ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ናቸው፤

የትምህርትና ስልጠና ... FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

12/ “የጥቅም ግጭት” ማለት በጥራት ኦዲት የግምገማ ሂደቱ ወይም ውጤቱ ላይ አሉታዊ ወይም አወንታዊ ተፅኖ ሊፈጥር የሚችል በተቋማት እና በጥራት ኦዲተሮች መካከል የተፈጠረ ግንኙነት ነው፤

13/ “ምክረ ሀሳብ” ማለት በጥራት ኦዲት ግኝቱ መሠረት ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዬች ላይ በባለስልጣኑ የሚሰጡ የማስተካከያ አቅጣጫዎች ናቸው፤

14/ “ሙሉ ለሙሉ የሚሠራ የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት” ማለት በእያንዳንዱ የጥራት ኦዲት ስታንዳርዶች ስር የሚገኙ አብዛኞቹ የጥራት ኦዲት ጋይድላየኖች ሙሉ ለሙሉ ተሟልተው ሲገኙ እና ጥቂት ጋይድላየኖች ብቻ በከፊል የተሟሉ ሲሆን የጥራት ኦዲት ለተከናወነበት የከፍተኛ ትምህርት ወይም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የሚሰጥ የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት የውጤታማነት ደረጃ ነው፤

15/ “የተሟላ የውስጥ ጥራት አጠባቅ ስርዓት” ማለት በእያንዳንዱ የጥራት ኦዲት ስታንዳርዶች ስር የሚገኙ አብዛኞቹ የጥራት ኦዲት ጋይድላየኖች ተሟልተው ሲገኙ እና ጥቂት የጥራት ጋይድላየኖች ብቻ የተጓደሉ ሲሆን የጥራት ኦዲት ለተከናወነበት ተቋም የሚሰጥ የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት የውጤታማነት ደረጃ ነው፤

16/ “ውስን የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት” ማለት በእያንዳንዱ የጥራት ኦዲት ስታንዳርዶች ስር የሚገኙ አብዛኞቹ የጥራት ጋይድላየኖች ያልተሟሉ እንዲሁም የጥራት አጠባበቅ ስርዓቱ ውጤታማ ላልሆነ ተቋም የሚሰጥ የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት የውጤታማነት ደረጃ ነው፤

17/ “የእውቅና ግምገማ ደብዳቤ” ማለት በጥራት ኦዲት ሂደት አልፈው ሙሉ ለሙሉ የሚሠራ እና የተሟላ የውስጥ ጥራት አጠባቅ ስርዓት ውጤታማነት ደረጃ ላገኙ የከፍተኛ ትምህርት ወይም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ለእውቅና ግምገማ ብቁ መሆናቸውን የሚገልፅ ለተቋማቱ የሚሰጥ ደብዳቤ ነው፤

18/ “ዳግም ክትትል” ማለት በጥራት ኦዲት ሂደት አልፈው የውስጥ ጥራት አጠባቅ ስርዓታቸው ውጤታማ ባልሆኑ ወይም ውስን የጥራት አጠባበቅ ስርዓት ደረጃ ባላቸው ተቋማት ላይ የሚደርግ የክትትል ግምገማ ነው፤

FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ፣

ሀ) በኢትዮጲያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ ማንኛውም የመንግስት እና የግል እንዲሁም ከውጭ ለሚመጣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋምና የትምርት ፕሮግራም

ለ) በፌደራል ደረጃ ለተቋቋመ እና ከውጭ ሀገር ለሚመጣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት

ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

Draft

ትምህርትና ስልጠና
FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

## ክፍል ሁለት

## ስለ ውስጥ ጥራት ማጎልበቻ ስርአት፣ የጥራት ኦዲት ቅድመ ሁኔታዎች እና የጥራት ኦዲት መገምገሚያ ስታንዳርዶች

4/ የተቋማት  የውስጥ ጥራት ማጐልበቻ

ሀ) ማንኛውም ተቋም በየጊዜው የሚሻሻል የውስጥ ጥራት ማጐልበቻ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፤

ለ) ማንኛውም ተቋም በባለስልጣኑ የተለዩ ጠንካራ ጎኖችን የመጠበቅ ወይም የማሻሻል እና የተሰጡ ምክረ ሀሳቦችን መተግበር ይኖርበታል፡፡

5/ የጥራት ኦዲት ጥያቄ ለማቅረብ መሟላት የሚኖርባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

የጥራት ኦዲት ጥያቄ በተቋም ወይም በፕሮግራም ደረጃ የሚያቀርብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም በተቋም ደረጃ የሚያቀርብ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ሀ እና ለ ስር ከተዘረዘሩት ውስጥ አግባብነት ባለው አካል ትምህርት ወይም ስልጠና ለመስጠት የተቋቋመ ወይም  ፈቃድ ያለው፤

ለ)  ቢያንስ አንድ ዙር ተማሪዎችን ያስመረቀ፤

ሐ) ለጥራት ኦዲት እንዲዘጋጅ ከባለስልጣኑ ደብዳቤ የደረሰው ወይም ለእውቅና ግምገማ ያመለከተ፤

መ) የከፍተኛ ትምህርት የፕሮግራም ጥራት ኦዲት እንደ አስፈላጊነቱ በባለስልጣኑ ተነሳሽነት ወይም በተቋማት ጥያቄ መሠረት ይሆናል፡፡



FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

6/ የጥራት ኦዲት መገምገሚያ ስታንዳርድ

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊም ሆነ የፕሮግራም እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተቋማዊ የጥራት ኦዲት ግምገማ ባልሰለጣኑ በሚያወጣው ሰታንዳርድ እና ውጤት አመላካቾች መሰረት ይከናወናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጥራት ኦዲተሮች ምልመላና የቡድን አወቃቀር

7/ ስለ ውጭ ጥራት ኦዲተሮች ምልመላ እና ምደባ

ሀ) የውጪ ጥራት ኦዲተሮች የሚመለመሉት ከትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ወይም ከሙያ ማህበራት ወይም ከኢንዱስትሪ ወይም ከጥናትና ምርምር ተቋማት ሊሆኑ ይገባል፤

ለ) በዚህ ክፍል በፊደል ሀ ስር ከተዘረዘሩ ተቋማት ባለሙያዎች የሚመለምሉት ባለስልጣኑ ባስቀመጠው የመመልመያ መስፈርት መሠረት መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) የጥራት ኦዲት ግምገማ ላይ የሚሳተፉ የውጭ ኦዲተሮች የኦዲተርነት ስልጠና የወሰዱ ብቻ መሆን አለባቸው፤

መ) የውጭ ኦዲተሩ ለኦዲተርነት ሲመለመል ኦዲት ከሚደረገው ተቋም ጋር የጥቅም ግጭት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

ሠ) የውጭ ኦዲተሮች ምልመላ እና ምደባ ባለስልጣኑ በሚያወጣው የጥራት ኦዲተሮች መረጣና ምልመላ ማንዋል መሰረት ይሆናል፡፡

8/ የጥራት ኦዲት ቡድን አወቃቀር

ሀ) ተቋማዊም ሆነ የፕሮግራም የጥራት ኦዲት ቡድን በአንድ የባለስልጣኑ ባለሙያ የሚመራ ሆኖ አራት የውጭ የጥራት ኦዲተሮችን የሚያካትት ይሆናል፤

ለ) የጥራት ኦዲቱ የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ላይ የሚከናወን ከሆነ የሚሳተፉት የውጪ ጥራት ኦዲተሮች ኦዲት የሚደረገው የትምህርት መስክ ባለሙያዎች ብቻ ይሆናሉ፤

ሐ) የጥራት ኦዲት ቡድን አባላት ተግባርና ሃላፊነት ባለስልጣኑ በሚያወጣው የጥራት ኦዲተሮች መረጣና ምልመላ ማንዋል መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡



FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

## ክፍል 4

## የጥራት ኦዲት አተገባበረ ሂደት

9/ ስለ ግለ ግምገማ

ሀ) ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በባለስልጣኑ የጥራት ኦዲት ስታንዳርድ መሰረት በየጊዜው በተቋም ወይም በፕሮግራም ደረጃ ግለ-ግምገማ ማካሄድ ያለበት ሆኖ ለባለስልጣኑ የሚያቀርበው ግለግምገማ ሪፖርት ለኦዲት ማመልከቻ ባቀረበበት ዓመት ያዘጋጀውን መሆን ይኖርበታል፤

ለ) በአንቀጽ 3 ፊደል ለ ስር የተገለጹት ተቋማት በባለስልጣኑ የጥራት ኦዲት ስታንዳርድ መሰረት በየጊዜው በተቋም ደረጃ ግለ-ግምገማ ማካሄድ ያለባቸው ሆኖ ለባለስልጣኑ የሚያቀርቡት ግለግምገማ ሪፖርት ለኦዲት ማመልከቻ ባቀረበበት ዓመት ያዘጋጀውን መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) ተቋማት ግለ ግምገማ የሚያደርጉት ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው የግለ ግምገማ ጋይድ ላየን መሰረት መሆን ይኖርበታል፤

መ) ተቋማዊም ሆነ የፕሮግራም የግለ ግምገማ ሪፖርት ሁሉንም ካምፓሶች ባካተተ መልኩ በተቋም ደረጃ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

ሠ) የግለ ግምገማ ሪፖርት በባለስልጣኑ እና በውጭ ኦዲተሮች ሚስጥራዊነቱ የተጠቀበ መሆን ይኖርበታል፤

ረ) ተቋሙ ያቀረበው የግለ ግምገማ ሪፖርት ማስተካከያ የሚያስፈልገው ከሆነ ምላሽ በተሰጠው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስተካክሎ ማቅረብ ይኖርበታል፤ በተሠጠው የጊዜ ገደብ አስተካክሎ ካላቀረበ የኦዲት ጥያቄውን በራሱ ፈቃድ እንዳቋረጠ ይቆጠራል፤

ሰ) የማንኛውም ተቋም የግለ ግምገማ ሪፖርቱ ተቀባይነት ባገኘ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ የጥራት ኦዲት ግምገማ መደረግ ይኖርታል፤



FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

10/ ቅድመ ጥራት ኦዲት

ሀ) ተቋማት ስለ ትምህርትና ስልጠና ጥራት አጠባበቅ ስልጠና ከጠየቁ ባለስልጣኑ ስልጠናውን መስጠት

ለ) ከሚገመግሙት ተቋም ጋር የጥቅም ግጭት ያለባቸው የውጭ ኦዲተሮች የጥራት ኦዲቱ እንዲያከናውኑ ሊመደቡ አይገባም፤

ሐ) በማንኛውም ተቋም የጥራት ኦዲት ጉብኝት ከመደረጉ በፊት ስለጥራት ኦዲቱ ገለፃ ሊደረግ ይገባል፡

11/ የጥራት ኦዲት ስለማከናወን

ሀ) ተቋማዊም ሆነ የፕሮግራም የጥራት ኦዲት በተቋም ደረጃ የሚደረግ ሆኖ ተቋሙ ከአንድ በላይ ካምፓሶች የሚኖሩት ከሆነ በተመረጡ ካምፓሶች ጥራት ኦዲት መደረግ የሚኖርበት ሆኖ ባለስልጣኑ በሚያወጣው ካምፓሶችን የመምረጫ መስፈርት መሰረት ይመረጣሉ፤

ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ ባለስልጣኑ ከጥራት ማስጠበቂያ የትኩረት መስኮች ውስጥ አንዱ ወይም የተወሰኑት ላይ ብቻ መሰረት በማድረግ የጥራት ኦዲት ሊያከናውን ይችላል፤

መ) የጥራት ኦዲት ቡድኑ በተቋሙ የቀረበውን የግለ ግምገማ ሪፖርት ትክክለኛነት ሰነዶችንና መረጃዎችን በመመርምር፤ ከተቋሙ ማህበረሰብ ጋር በመወያየት እና በአካል ምልከታ በማድረግ መረጃ መሰብሰብና ማጠናቀር ይኖርበታል፤

ሠ/ ተቋሙ በጥራት ኦዲት ቡድኑ የሚጠየቁ መረጃና ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፤

12/ የጥራት ኦዲት ሳይክል(ዑደት)

ሀ) የአንድ ለእውቅና ግምገማ ብቁ የሚያደርግ ደብዳቤ ለ 5 ዓመታት ብቻ ያገለግላል፣

FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

## ክፍል 5

## የጥራት ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት ዝግጅት

### 13/ የሪፖርት ዝግጅት

ሀ) በእያንዳንዱ ጋይድላይን እና ውጤት አመላካች መረጃ ሊሰበሰብበትና የተሰበሰበ መረጃ ሪፖርት ሊጠናቀርበት ይገባል፤

ለ) የተሰበሰበው መረጃ በእያንዳንዱ ጋይድላይን እና ውጤት አመላካች ተገምግሞ ጠንካራ ጐኑ ሊገለፅ ወይም ምክረ ሀሳብ ሊሰጥበት ይገባል፤

ሐ) ሪፖርቱ በባለስልጣኑ የጥራት ኦዲት ሪፖርት አጻጻፍ ቅጽ መሰረት ብቻ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

መ) ረቂቅ ሪፖርቱ ተቋሙ ግብረ መልስ እንዲሰጥበት መላክ ይኖርበታል፤

ሠ) ተቋሙ የተላከለት ረቂቅ ሪፖርት ላይ ግብረ መልስ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለባለስልጣኑ ካላሳወቀ ሪፖርቱን ሙሉ ለሙሉ እንደተቀበለው ይቆጠራል፤

Draft

FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

## ክፍል 6

### የክትትል ግምገማ፣ የጥት ኦዲት ሪፖርት፣ ህትመት እና የእውቅና ግምገማ ደብዳቤ

14/ ስለጥራት ኦዲት ክትትል ግምገማ

ሀ) የጥራት ኦዲት ሪቂቅ ሪፖርቱ ለተቋሙ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በተቋም ደረጃ የተዘጋጀ የጥራት ማጎልበቻ እቅድ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፤

ለ) ተቋሙ የጥራት ማጎልበቻ እቅድ ባቀረበ በ 3 ወራት ጊዜ ውስጥ የክትትል ግምገማ መደረግ ይኖርበታል፤

ሐ) ተቋሙ ከአንድ በላይ ካምፓሶች የሚኖሩት ከሆነ በተመረጡ ካምፓሶች የክትትል ግምገማ የሚደረግ ሆኖ ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ካምፓሶችን የመመምረጫ መስፈርት መሰረት ካምፓሶች የሚመረጡ ይሆናል፤

15/ የጥራት ኦዲት ሪፖርት ህትመት

ሀ/ የጥራት ኦዲት ሪፖርቱ በባለስልጣኑ እስኪታተም ድረስ ሚስጥራዊነቱ ሊጠበቅ ይገባል፤

ለ/ የፀደቀው ሪፖርት በባለስልጣኑ ተደራሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡

16/ የጥራት ኦዲት አፈፃፀም ደረጃዎች

ሀ) ተቋማት በጥራት ኦዲት ስታንዳርድ ተገምግመው ሙሉ ለሙሉ የሚሠራ፣ የተሟላ ወይም ውስን የውስጥ ጥራት አጠባቅ ስርዓት ያላቸው በመባል በሦስት የውስጥ ጥራት አጠባበቅ የውጤታማነት ደረጃዎች ይመደባሉ፡

ለ/ ሙሉ ለሙሉ የሚሠራ እና የተሟላ የውስጥ ጥራት አጠባቅ ስርዓት ያላቸው ተቋማት በቀጥታ የእውቅና ግምገማ ጥያቂ ለማቅረብ ብቁ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ የሚሰጣቸው ይሆናል፤



FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

ሐ/ ውስን የውሰጥ ጥራት አጠባቅ ስርዓት ያላቸው ተቋማት የተሟላ የውስጥ ጥራት አጠባቅ ስርዓት ደረጃ ላይ እስኪደርሱ ድረስ የዳግም ክትትል ግምገማ ይደረጋል፡፡

## <u>ክፍል 7</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

17/ **የቅሬታ አቀራረብና አፈታት**

በዚህ መመሪያ፣ በከፍተኛ ትምህርት እና በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ስታንዳርዶች መሰረት የጥራት ኦዲት ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው የትምህርትና ስልጠና ተቋም የኦዲት ሪፖርቱ ተደራሽ በሆነ በ 30 ቀን ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

18/ **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህን መመሪያ ትምህርት ሚኒስቴር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

19/ **መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ሚኒስቴር ድረ ገፅ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ከሆነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

ትምህርትና ስልጠና
FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY